??? ??? ?? ?? ?? 2? ??? ? ? ??? ???
?? ???? ? ??? ?? ? ? ? ?? ? ???? ? ? ???
??? ? ????? ? ??

?

በጎሰው የሸዋስ

(begosew12@gmail.com)

? ??? 6 ?? 2007 ?.?

??? ???

1. መግቢያ

“የትኛውም መምህር ቢሆን በማስተማር ብቃቱ ሙሉ አይደለም፡፡” በማለት CullingFord (1995፡11) ይገልጻሉ፡፡ ሆኖም ግን ከጀማሪ መምህራን /Novice teachers/ ነባር መምህራን /Experienced teachers/ በአንጻራዊ መልኩ በተሻለ ሁኔታ እንደሚያስተምሩ የተለያዩ ምሁራን ቢገልጹም፤ ሌሎቹ ደግሞ ጀማሪዎቹ ከነባሮቹ በተሻለ ሁኔታ ስለማስተማራቸው የመከራከሪያ ሐሳብ እንደሚያቀርቡ Amera (2005፡8) ይገልጻሉ፡፡ መምህራን የማስተማር ልምድ እያካበቱ ሲሄዱ ቀስ በቀስ የትኛው የማስተማር ዘዴ ጥሩ እንደሆነ በመረዳት ተገቢውን ትምህርት ለተማሪዎች ይሰጣሉ (Cullingford 1995፡161)፡፡ ይህም መምህራን በኮሌጅ ቆይታቸው ያላወቁትን እና ያልተገነዘቡትን ስልት በማስተማር ተሞክሮ መገንዘባቸው እና ማወቃቸው ነው በማለት ያስረዳሉ፤ በአንጻሩ Wingard (1974፡46) ግን ይህን ሐሳብ አይቀበሉም፡፡ “ልምድ እየጨመረ ሄደ ማለት የመምህሩ እድሜም እየጨመረ ሄደ ማለት ነው፤ በመሆኑም የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴውም በዚያው ልክ እየቀነሰ ይሄዳል፡፡” በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ በቀደምት ጥናቶች የማስተማር ልምድ ለውጤታማ የመማር-ማስተማር ሂደት ጠቀሜታው የጎላ ነው በሚል ሲታመንበት ቆይቷል፡፡ በዚህ ዘመን ግን ይህ ሐሳብ የተገላቢጦሽ እንደሆነ Amera (2005፡8) ይገልጻሉ፡፡ ለዚህም በማሳያነት የሚያነሱት Johnston /1994/ “አንድ መምህር ብዙ አመት የማስተማር ልምድ ስላለው በጥሩ ሁኔታ ያስተምራል ብሎ ማመን በራሱ ከጭፍንነት /Blind faith/ የመነጨ ነው፡፡” በማለት ይገልጻሉ፡፡ይህን ሐሳብ Duke (1990) ሲያጠናክሩት “ልምድ ብቻውን የአንድ ጥሩ መምህር መገለጫ አይደለም በማለት ልምድ ትርጉም እንዲኖረው ያለፉት የሥራ ዓመታት የተለያዩ ጥናት እና ምርምሮች በማካሄድ እና በመመልከት የራስን አተገባበር በመፈተሽ ያለፈ ከሆነ ብቻ ነው፡፡” በማለት የማስተማር ልምድ ምንነት እና ጠቀሜታ ይገልጻሉ፡፡

ጥናቱ የሚያተኩረው በነባር መምህራን ማለትም ከአስር ዓመት በላይ ባስተማሩ እና ከአምስት ዓመት በታች ባስተማሩ ጀማሪ መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርት አተገባበር ላይ ነው፡፡ አንድ መምህር ነባር ወይም የልምድ ባለቤት ነው በሚል አጥኚው ከ10 ዓመት በላይ ያስተማሩ መምህራንን የመረጠበት ምክንያት “አንድን መምህር በማስተማር ልምዱ የተነሳ ውጤታማ አስተማሪ መሆኑን ወይም አለመሆኑን የምንገመግመው ቢያንስ ለ10 ዓመት ካስተማረ በኋላ ነው” Marsh /2007:775/፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የጀማሪ መምህራንን ከአምስት ዓመት በታች የአስተማሩ በሚል አጥኚው የወሰነበት ምክንያት Smith /1982:368/ የማሰተማር ልምድን በአምስት ደረጃ ከፋፍለው የአስቀመጡትን መሠረት በማድረግ ነው። ይኸውም፣ <5፣ 5-10፣ 11-15፣ 16-20 እና >20 ናቸው። ስለሆነም ዝቅተኛው የማስተማር ጊዜው ወይም ዓመት ከአምስት ዓመት በታች ልምድ ያላቸው መምህራን የሚል ስለሆነ በዚሁ መልክ የተወሰደ ነው።

የዚህ ጥናት ዓላማም ንባብን እንደ ጥናት መሳሪያ በመጠቀም፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በነባር መምህራን እና በጀማሪ መምህራን መካከል ያለውን የቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ በንፅፅር መቃኘት ሲሆን፣ በተጨማሪም በጥናቱ የቋንቋ ትምህርትን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተሳካ መንገድ ለመካሄድ እንቅፋት የሆኑ ተላውጠዎች ምን እንደሆኑ ለመፈተሽ ተሞክሯል። ለጥናቱ አስተማማኝ መረጃዎችን ለማግኘት ዓይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴዎች ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችም የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ የጽሑፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ናቸው።

2. ቋንቋን በማስተማር ሂደት የውጤታማ መምህር ምክንያት እና መገለጫ

ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል በመገኘት ለሚያመጡት የሥነልቦና እና የሥነ አእምሮ ለውጥ የመምህሩ ውጤታማነት እና ብቃት ወሳኝ ነው። ውጤታማ-መምህር በውጤታማ የመማር-ማስተማር ሂደት እና የትምህርት ውጤት ሊገለጽ እንደሚችል የታመነ ነው። የውጤታማ መማር-ማስተማር ሂደት መገለጫዎችም የሚከተሉት እንደሆኑ Mesafint (1999፡20) NPQTL (1993)ን በመጥቀስ የሚከተሉትን ይዘረዝራሉ፤

- በመማር-ማስተማሩ ወቅት ያለው የመምህራን እና የተማሪዎች ግንኙነት፣
- የመምህሩ የማስተማር ልምድ፣
- ለትምህርት የቀረበው የትምህርት ይዘት፣
- የመማር-ማስተማሩ የክፍል ውስጥ ተግባራት፣
- የክፍል ውስጥ የቁጥጥር ሁኔታ፣
- መምህሩ ስለሚያስተምረው ትምህርት ያለው ዕውቀት፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከላይ ከተዘረዘሩት የውጤታማ መማር-ማስተማር ሂደት መገለጫዎች መካከል በመማር-ማስተማሩ ሂደት በመምህሩ እና በተማሪዎች መካከል የሚኖረው ግንኙነት አንዱ ነው። ምክንያቱም መምህራን ከተማሪዎች ጋር የሚኖራቸው ጤናማ ወይም ጤናማ ያልሆነ ግንኙነት ነው በመማር-ማስተማር ውጤታማነት ላይ ውድቀትን ወይም ስኬትን ሊያመጣ የሚችለው በማለት Azeb (1984፡56) ይገልጻሉ። ይህን ሐሳብ በሚያጠናክር መልኩ Nunan (1992፡63) በተማሪዎች እና በመምህሩ መካከል መልካም ግንኙነት ካለ ተማሪዎች በነጻነት ምን እንደሚማሩ፣ ስለምን እንደሚማሩ እየተከታተሉ ይጠይቃሉ፤ የሚሰጣቸውንም ትምህርት በደስታ ይቀበላሉ በማለት ይገልጻሉ። በመሆኑም መምህሩ በቅድሚያ ከተማሪዎች ጋር መልካም ግንኙነትን እና ተግባቦትን ፈጥሮ ትምህርቱን የሚሰጣቸው ከሆነ የመማር-ማስተማሩ ሂደት የሚከተሉት መልኮች ይኖሩታል (Crouch 1989፡106)፤

- በመማር ማስተማሩ ወቅት በተማሪዎች መካከል ጥሩ የሆነ ግንኙነት እና ውይይት ይኖራል፤
- በመማር ማስተማሩ ሂደት ያልተገባ ጫጫታ እና ሁካታ አይኖርም፤
- ተማሪዎች በጥሞና ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ይስተዋላል፤

- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰጣቸውን ተግባራት በሙሉ ፈቃደኝነት ይሰራሉ፤
- ትምህርቱ ተማሪዎችን በሚያስጨንቅ መንገድ ሳይሆን ተማሪዎችን በሚያዝናና መልኩ ይቀርባል፤
- ትምህርቱ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ የተማሪዎች ትኩረት በትምህርቱ ላይ ብቻ ይሆናል።

በመሆኑም የውጤታማ ትምህርት መሠረቱ ውጤታማ መምህር እንደሆነ፤ የውጤታማ መምህር መገለጫዎች ደግሞ ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደሆኑ ተገልጽዋል። እነዚህን መገለጫዎች በሦስት ዓበይት ክፍሎች ጠቅለል ብለው ሊገለጹ እንደሚችሉ Dawite (2000፡22) Fuller (1969)ን በመጥቀስ ያስረዳሉ። አንደኛ የመምህሩ አካዳሚያዊ ብቃት /Self concern/ አንዱ ነው። አካዳሚያዊ ብቃት ሲባል፣ መምህሩ ስለሚያስተምረው የትምህርት ዓይነት በቂ ዕውቀት ያለው መሆኑን እና በመማር-ማስተማሩ ሂደት ያለው የራስ መተማመን ዋና ዋና መገለጫዎቹ እንደሆኑ ያብራራሉ። ሌላው የመምህሩ የክፍል ውስጥ አተገባበር /Task concern/ ሁለተኛ መገለጫ ነው። የክፍል ውስጥ አተገባበር ሲባል ደግሞ የመምህሩ ለማስተማሪያነት የተዘጋጁ መሣሪያዎችን የመጠቀም ብቃት፣ ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው አጋዥ መሳሪያዎችን የመጠቀም ልምድ፣ የተስተካከለ የክፍል ውስጥ ቁጥጥር፣ ትምህርቱን በተመደበው ሰዓት የመጨረስ ብቃት እና ለተማሪዎች ይጠቅማሉ የሚላቸውን ተዛማጅ ነገሮች በማምጣት ለተማሪዎች ሰፊ ዕውቀት ማስጨበጥን ይመለከታል። ሦስተኛው እና የመጨረሻው መገለጫ የመምህሩ እና የተማሪዎች ግንኙነት /Students concern/ ነው። ተማሪዎች እንደ አደጉበት አካባቢ፣ ባህል እና የኢኮኖሚ ደረጃ የትምህርቱ አሰጣጥ ከግንዛቤ መግባት አለበት። በመሆኑም የተማሪዎችን ዳራዊ ልምድ እና ተገቢ የማስተማር ዘዴ፣ የማስተማሪያ መሣሪያዎች እና የተማሪዎች የመማር ፍላጎት፣ መቼ; የትኛውን ትምህርት መስጠት ይመረጣል፣ ወዘተ. የሚሉ ነጥቦችን ከግንዛቤ አስገብቶ የሚያስተምር መምህር ውጤታማ መምህር ሊባል ይችላል በማለት Dawite (2000፡23) ያስገነዝባሉ።

“የአንድ መምህር ውጤታማነት የሚመነጨው መምህሩ ለሙያው ካለው ፍቅር ነው” በማለት Azebe (1984፡40) ይገልጻሉ። የሙያ ፍቅር እና ተነሳሽነት ደግሞ የሚመጣው መምህር የማስተማር ልምድ እያካበተ ሲሄድ ነው በማለት Underhill /1989፡252/ እና Hussen (2010፡16) Rabinowitz and Rosenbaum (1960)ን በመጥቀስ ይገልጻሉ። በመሆኑም የማስተማር ልምድ /Teaching experience/ አንዱ የውጤታማ ትምህርት

መገለጫ እንደሆነ መግንዘብ ይቻላል። በምክንያትነት Yohannes (2005፡32), Caillods (989)ን በመጥቀስ ሲገልጹ፣ በመማር-ማስተማሩ ሂደት የክፍል ውስጥ ቁጥጥር እና አተገባበር ከኮሌጅ ቆይታ ከሚገኝ የንድፈ ሐሳብ እውቀት በበለጠ በማስተማር ልምድ የሚገኝ ዕውቀት ከፍተኛ በመሆኑ ነው በማለት ይገልጻሉ። ለዚህም ነው በአብዛኛዎቹ ታዳጊ ሀገራት፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከፍተኛ የሆነ የማስተማር ሙያና ልምድ ማነስ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለተፈጠረው የትምህርት ጥራት ችግር እንደ አንድ ምክንያት ሊገለጽ ይችላል በማለት Yohannes (2005፡32-33) ያስረዳሉ።

2.1 የማስተማር ልምድ እና የማስተማር ብቃት

ተማሪዎች መማር ስለሚገባቸው ትምህርት እና አሰጣጥ ዙሪያ መምህራን የተለያዩ አመለካከቶች እንዳሏቸው Mesafint (1999፡10) Stones (1994)ን በመጥቀስ እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

> ልምድ ያካበቱ መምህራን ማስተማር ማለት በጣም ውስብስብ የሆነ ተግባር እንደሆነ በማመን ለተማሪዎች መረጃ መስጠትን ብቻ ሳይሆን ጥናት እና ምርምር ማድረግ እና ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሔ ማፈላለግን ሁሉ እንደሚያጠቃልል አምነው ተማሪዎችን ችግር ፈች እና ተመራማሪ እንዲሆኑ ይጥራሉ። ከዚህ በተጨማሪ በመርሃ ትምህርቱ በቀረበው ትምህርት ብቻ ሳይወሰኑ ተዛማጅ ተጨማሪ ትምህርቶችን ያስተምራሉ። ጀማሪ መምህራን ግን ማስተማር ማለት በመርሃ ትምህርቱ የቀረቡላቸውን ነገሮች ብቻ በመናገር እና በማብራራት ብቻ የሚወሰን እንደሆነ እና ስራቸውም በመርሃ ትምህርቱ የቀረበውን ትምህርት መሸፈን አድርገው ይቆጥራሉ በማለት ይገልጻሉ።

በሌላ በኩል Amera (2005፡1) መምህራን የብዙ ዓመት የሥራ ልምድ ባለቤት እየሆኑ በሄዱ ቁጥር በትምህርታዊ ጥናት እና ምርምር ያላቸው ተሳትፎ ከጀማሪ መምህራን ያነሰ መሆኑን በጥናታቸው በማረጋገጥ ልምድ በጥናታዊ ምርምር ላይ ከአዎንታዊ ሚናው ይልቅ አሉታዊ ሚናው የጎላ ነው በማለት ገልጸዋል። ይህም አዳዲስ ነገሮችን ለመቀበል ካላቸው ተነሳሽነት እና ፍላጎት ሊሆን እንደሚችል አያይዘው ያስረዳሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ Redwan (2006) “በቡታጀራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያሉ መምህራን በፕላዝማ ቴሌቪዥን ትምህርት ዙሪያ ያላቸው አመለካከት” በሚል 39 መምህራን ወስደው

ባካሔዱት ጥናት ልምድ ያካበቱ መምህራን ከጀማሪ መምህራን በበለጠ አለታዊ አመለካከት እንዳላቸው አረጋግጠዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ Amera (2008) "በባሕርዳር ከተማ በሚገኙ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመምህራን የማስተማሪያ መሣሪያዎች አጠቃቀም ከማስተማር ልምድ አኳያ" በሚል 182 መምህራንን ወስደው ባካሂዱት ጥናት ብዙ ያስተማሩ ነባር መምህራን ከጀማሪ መምህራን ባነሰ ሁኔታ ሲጠቀሙ ማስተዋላቸውን በጥናታቸው አረጋግጠዋል። በመሆኑም ከእነዚህ ጥናቶች እንደምንመለከተው መምህራን የማስተማሪያ መሣሪያዎችን በአግባቡ ካልተጠቀሙ በተማሪዎች ዕውቀት እና ውጤት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደሆነ ነው።

Cullingford (1995፡162) እና Jeylan (1992፡38) Head and Taylor (1997) በመጥቀስ ከጀማሪ መምህራን ይልቅ ልምድ ያካበቱ መምህራን በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሣ በተሻለ ሁኔታ ያስተምራሉ በማለት ይገልጻሉ፤

ሀ. መምህራን ከራሳቸው የማስተማር ፍላጎት እና ስልት ይልቅ ለተማሪዎች የመማር አስተሳሰብ እና ምርጫ ትኩረት በመስጠታቸው፣

ለ. መምህራን የማስተማር ልምድ እያካበቱ በሂዱ ቁጥር የብዙ ማስተማሪያ ዘዴዎች ዕውቀት ባለቤት ይሆናሉ፤ ይህ ደግሞ የተማሪዎችን ማንነት ተገንዝበው ጥሩውን የማስተማሪያ ዘዴ እንዲከተሉ ያስችላቸዋል፣

ሐ. መምህራን በቂ ልምድ ካላቸው ተገቢውን እውቀት ለተገቢው የክፍል ደረጃ ለክተው ለመስጠት ያስችላቸዋል፣

መ. በሥልጠና ወቅት ያገኙትን ንድፈ ሐሳብ ከሚያስተምሩበት አካባቢ እና ከተማሪዎች ሁኔታ አኳያ እያስማሙ መሄዳቸው፣

ሠ. መማር በሂደት የሚገኝ እና የሚበለጽግ በመሆኑ በሥልጠና ወቅት ከተገኘ ዕውቀት በበለጠ በማስተማር ሂደት በማግኘታቸው ነው።

ከላይ ከተሰጡት ምክንያቶች መገንዘብ እንደሚቻለው መምህራን ብዙ የማስተማር ልምድ እያካበቱ በሂዱ ቁጥር የተሻለ ትምህርት ለተማሪዎች ሊሰጡ እንደሚችሉ ነው። በሌላ በኩል አዳዲስ መምህራን ስለሚያስተምሩት ትምህርት እንጂ ስለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች በቂ ዕውቀት ካለመያዛቸው የተነሣ እንደሆነ ከብዙዎቹ ምክንያቶች እንዳንድ ምክንያት ይጠቀሳል። ነገር ግን በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ ጀማሪ መምህራን የሚሰጡት ትምህርት ሁልጊዜ ብቃት የሌለው፣ ልምድ ያካበቱ መምህራን የሚሰጡት ትምህርት

ሁልጊዜ የተሻለ እና ጥሩ እንደሆነ መታሰቡ ፈጽሞ የተሳሳተ እንደሆነ Abiyot (2001፡2) ይገልጻለ፡፡ ምክንያቱንም አብዮት ሲያስረዱ፣ ሁሉም ባይሆኑ ወደ ሙያው እንደገቡ በጥሩ ሁኔታ ሲያስተምሩ ጀማሪ መምህራን በጥናት ተስተውሏል በማለት ይገልጻለ፡፡
በሌላ በኩል አንድ መምህር ብዙ ዓመት በሥራ ስለቆየ የተሻለ መምህር ነው ማለት አይቻልም በማለት Jeylan (2003፡36)፣ Johnson (1994) በመጥቀስ ይገልጻለ፡፡ ልምድ ትርጉም የሚኖረው መምህሩ ባስተማረባቸው ዓመታት አዳዲስ ነገሮችን በመማር ሂደት ካሳለፈ ብቻ ነው ሲሉ ይገልጻለ፡፡ ይህም ሲባል መምህሩ ባሳለፋቸው የማስተማር ዓመታት በምን ዓይነት መንገድ አስተምሮ፣ ምን ዓይነት ውጤት እንዳስመዘገበ ሲገመግም፣ በየጊዜው ከሚመጡ አዳዲስ የማስተማሪያ ዘዴዎች እና ዕውቀቶች ጋር በመተዋወቅ ካለፈ ልምድ በራሱ የዕውቀት ምንጭ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በእነዚህ ተግባራት ታጅቦ ካላለፈ ልምድ የዕውቀት ምንጭ መሆኑ ቀርቶ ትርጉም የለሽ ልማድ ይሆናል በማለት Jeylan (1992፡37)፣ Wajnryb (1992) እና Kolb (1984) በመጥቀስ ይገልጻለ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ Wingard (1974፡47) ሲገልጹ “መምህሩ በየጊዜው አዳዲስ ስልጠናዎችን ካልወሰደ አስር ዓመት ያስተማረ መምህር አንድ ዓመት ካስተማረ መምህር የሚሻልበት ምንም ምክንያት የለም” በማለት ልምድ በማስተማር ተግባር ትርጉም እንዲኖረው ሁልጊዜ በአዳዲስ ስልጠናዎች መታጀብ የግድ እንደሆነ የሚገልጹት፡፡

ጀማሪ መምህራን አዳዲስ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ከኮሌጅ እንደተመረቁ ይዘው በመውጣት በወቅታዊ የማስተማሪያ ዘዴ ሊያስተምሩ ሲችሉ፣ ነባሮቹ መምህራን ግን ለብዙ ዓመታት የተጠቀሟቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎች እንደ ልማድ በመውሰድ ለአዳዲሶቹ የማስተማሪያ ዘዴዎች ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደማይችሉ እና ፍላጎትም ላይኖራቸው ይችላል የሚል አተያይ በአንዳንድ ወገኖች እንዳለ Cullingford /1995:162/ ይገልጻለ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ Wingard (1974:48) ሲገልጹ፣ “መምህራን በማስተማር ሙያ ልምድ እያጎለበቱ ሲሄዱ ለማስተማር የሚመቻቸው ዘዴ ይህ ነው ብለው” ይወስናሉ፡፡ በዚህም የተነሣ በየጊዜው የሚመጡ አዳዲስ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ውድቅ ሲያደርጉ ይስተዋላል፡፡ ይህን ሐሳብ Stern (1983:24) ሲያጠናክሩ፣ “ብዙ ጊዜ ከጀማሪ መምህራን ይልቅ ለብዙ ጊዜ ቋንቋን በማስተማር የቆዩ መምህራን አዳዲስ ሳይንሳዊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተቀብለው ከመተግበር ይልቅ በጥርጣሬ መመልከትን ይመርጣሉ” በማለት ይገልጻለ፡፡

በሌላ በኩል መምህራን ልምድ እያካበቱ በሄዱ ቁጥር የተሻለ የማስተማር ስልት ግንዛቤ ይኖራቸዋል የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ ይህ ደግሞ በተለያዩ ጊዜያት የሚመጡ አዳዲስ የማስተማር ትውረቶችን አዲስ ስለሆኑ ብቻ ከመቀበል፤ እኔ ለማስተምረው አካባቢ እና ተማሪዎች ይመቻል ወይስ አይመችም የሚለውን አመለካከት ለመፈተሽ ብቃቱ ይኖራቸዋል በማለት Palmer (1993:166) ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መምህራን ልምድ እያካበቱ በሄዱ ቁጥር የክፍል ውስጥ ቁጥጥራቸው እና ተማሪዎችን የማነሳሳት አቅማቸው የተሻለ እየሆነ ይመጣል በማለት Reda (2005:58) ይገልጻሉ፡፡

3. የመረጃ አሰባሰብ እና ትንተና

3.1 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን ያገለገሉት የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ የጽሁፍ መጠይቅ እና ቃለመጠይቅ ናቸው። የክፍል ውስጥ ምልከታው የተከናወነው ተጠኚ መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት በውስን /fixed/ የምልከታ ስልት ነው። ውስን ምልከታን ለማከናወን የተለያዩ ሞዴሎች እንዳሉ Sheal (1989) ከዘረዘሯቸው መካከል የማረጋገጫ ዝርዝር (check list) አገልግሎት ላይ ውሏል።

ሌላው ለመረጃ መሰብሰቢያነት ከዋሉት መሣሪያዎች መካከል ተጠኚ መምህራን የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች የሞሉት የጽሑፍ መጠይቅ ሲሆን፣ መጠይቁም ክፍት እና ዝግ ጥያቄዎችን ያካተተ ነው።

ከጽሑፍ መጠይቅ እና ምልከታ በተጨማሪ ቃለ መጠይቅም የዚህ ጥናት አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ በመሆን አገልግሏል። ይህ መጠይቅም ለተጠኚ መምህራን፣ ለአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት ኃላፊዎች እና ለአስተዳደር አካላት የቀረበ ነው። ለተጠኚ መምህራን የቀረቡ ጥያቄዎች የቋንቋ ትምህርትን በአግባቡ በክፍል ውስጥ ለማከናወን እንቅፋት የሆኑ ተላውጦዎችን እና መፍትሔዎቻቸውን ለመሰብሰብ የተዘጋጁ ናቸው።

3.2 የናሙና አመራረጥ

በናሙና የተመረጡት የመረጃ ምንጮች ትምህርት ቤቶች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ የአማርኛ ቋንቋ ክፍለትምህርት ኃላፊዎች እና የአስተዳደር አካላት ናቸው።

3.2.1 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የሚከናወነው በአዲስ አበባ ክልላዊ መስተዳደር ነው። የጥናቱ ክልል የተመረጠው አጥኚው መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ወካይ ናሙና በዓይነትም ሆነ በመጠን ከሌሎች ክልሎች በተለየ በዚህ ክልል በበቂ ሁኔታ ይገኛል ብሎ ስላመነ ነው። በዚህ መስተዳድር ሥርም ብዙ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። ቢሆንም ግን ከጊዜ፣ ከገንዘብ፣ ከቁሳቁስ እና ከሰው ኃይል ውስንነት አኳያ ለጥናቱ የሚሆኑ አራት ትምህርት ቤቶች በዕጣ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል። ትምህርት ቤቶቹ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የሚገኙ

ሲሆን እነዚህም ፊታአውራሪ ዓባይነህ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ቡልቡላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በሰቃ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ቃሊቲ ሁለተኛ ደረጃ ትምህረት ቤት ናቸው፡፡ በእነዚህ ትምህርት ቤቶችም በ10ኛ ክፍል ደረጃ የሚያስተምሩ መምህራንና የሚማሩ ተማሪዎች የጥናቱ ተተኳሪዎች እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ ይህም የተደረገው የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ እና የመምህራኑ አተገባበር በጥናቱ ተተኳሪዎች መካከል የሚፈጥረውን ተጽዕኖ ቀድሞ ለመከላከል በማሰብ ነው፡፡

3.2.2 የተጠኚ መምህራን ናሙና አመራረጥ

በዕጣ የንሞና ዘዴ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ መምህራን እንደ ልምዳቸው በሁለት ምድብ ከተከፈሉ በኋላ በእድል ሰጪ የንሞና ዘዴ ማለትም በእጣ እንዲመረጡ ተደርጓል፡፡ ይኸውም የተከናወነው የመምህራን አጠቃላይ ዳራ ከየትምህርት ቤቶቹ የትምህርት አስተዳደር ከተወሰደ በኋላ መምህራን ባሳለፏቸው የስራ ዓመታት የወሰዷቸው አዳዲስ ሥልጠናዎች እና የትምህርት ደረጃዎችን ከፍ ለማድረግ የወሰዱት “ኮርስ” ካለ በቅድሚያ የማጣራት ስራ በጥንቃቄ ተከናውኗል፡፡ በመጨረሻም ሁሉም በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቁ እና በአማርኛ ቋንቋ አፈፈት የሆኑ መምህራን የጥናቱ አካል እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ከሁሉም ትምህርት ቤቶች ለጥናቱ የሚመጥኑ እና የሚስማሙ አራት ነባርና አራት ጀማሪ መምህራን በአጠቃላይ ስምንት መምህራን በናሙናነት ተወስደዋል፡፡

3.2.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ከአራቱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመማር ላይ ከሚገኙት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል ተጠኚ መምህራን በሚያስተምሩባቸው በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ውስጥ በአማካይ ከ50-60 ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል በእያንዳንዱ ምልከታ በተካሄደባቸው ክፍሎች ወካይ የሚሆኑ ተማሪዎችን አንድ ሦስተኛ (35%) በመውሰድ በአጠቃላይ 160 ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቁን ሞልተው መልሰዋል፡፡ ነገር ግን የጽሑፍ መጠይቁን ከሞሉ ተማሪዎች መካከል ሰባቱ በትክክል ስላልሞሉ 153ቱ ብቻ ለትንተና ውለዋል፡፡

3.3 የመረጃ ትንተና

በምልከታ፣ በጽሑፍ መጠይቅ እና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደተሰበሰቡበት ስልት “የነባርና የጀማሪ መምህራን” በሚል ተደራጅተዋል። ከሁለቱ የጥናቱ ተተኳሪ ቡድኖች በተለያዩ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በየንዑስ ርዕሰ ጉዳዮች ሥር በመደራጀት እየተነጻጸሩ ተተንትነዋል።

በቅድሚያ በምልከታ የተሰበሰቡ የነባርና የጀማሪ መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርት ክንውን ድግግሞሽ አማካይ (mean) ውጤት ተሰልቷል። በአማካይ ውጤት መካከል ያለውን የጉልህነት ደረጃ ለማወቅ በ “t-test” ስሌት ተሰልተዋል።
በጽሑፍ መጠይቁ በሁለት ዓይነት መንገድ መረጃዎች ተሰብስበዋል። የመጀመሪያው በአራት የስምምነት ስኬሎች (ዘወትር፣ አብዛኛውን ጊዜ፣ አንዳንድ ጊዜ ያከናውናሉ እና ፈጽሞ አያከናውኑም) በሚል የቀረቡ ሲሆን፣ በዚህ መንገድ የተገኙ መረጃዎች በተናጠል በንጽጽር ተተንትነዋል። ከትንተናው በኋላ ዘወትርና አብዛኛውን ጊዜ ያከናውናሉ የሚሉት በአንድ ወገን፣ ፈጽሞ አያከናውኑም የሚሉት በሌላ ወገን እየተሰሉ ለጥናቱ ተተኳሪዎች ውሳኔ መስጫነት ውለዋል። ሌላው ክፍት የጽሑፍ መጠይቅ ጥያቄዎች በየርዕሰ ጉዳዮች ስር በመቀናጀት ተተንትነዋል።

በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎችም እንዲሁ በአግባቡ ተተንትነዋል። ከመምህራን ጋር የተካሄዱ የቃል መጠይቆች፣ ከምልከታና ከጽሑፍ መጠይቁ ጋር በየርዕሰ ጉዳዮች ስር በመቀናጀት በገለጻ ሲተነተኑ፣ ከአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት ኃላፊዎች እና ከአስተዳደር ሰራተኞች ጋር የተካሄዱ የቃል መጠይቆች ደግሞ በስተመጨረሻ በተናጠል በገለጻ ተተንትነዋል።

4.ማጠቃለያና አስተያየት

4.1 ከአይነታዊ መረጃዎች የተገኘ ውጤት

- በሁለቱም ወገን ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ያሉ ቢሆንም፣ በአንጻራዊ መልኩ ግን ነባር መምህራን ተመራጭ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች ነባር መምህራን ያለበትን ምክንያት ሲያስረዱ፣ ነባር መምህራን ዓመታዊ እና ሳምንታዊ እቅዶችን በአግባቡ ከመስራት፤ የተማሪዎችን ማንነት እና የክፍል ደረጃ ያገናዘበ ትምህርት በክፍል ውስጥ ከመስጠት፤ ከክፍል ውስጥ ቁጥጥር፤ በአንጻራዊ መልኩ ለስራቸው ካላቸው ፍቅር እና መረጋጋት አኳያ፤ ለሁሉም የቋንቋ ክሂሎች ተገቢ ትኩረት ከመስጠት፤ ትምህርቱን በእናታዊ እና አባታዊ አንደበት በቀልድ እያጀቡ ከማቅረብ፤ ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ ጥሩ ገለፃ ከማካሄድ፤ የተማሪዎችን ችግር ከመረዳት፤ የተለያዩ አጋዥ መፅሐፍትን ከመጠቀም አኳያ ነባር መምህራን ከጀማሪ መምህራን የተሻሉ እንደሆኑ ታውቋል፡፡
- አብዛኛውን ጊዜ ጀማሪ መምህራን በኮሌጅ ቆይታቸው የተማሩትን ሁሉ ለተማሪዎች ሳይመጥኑ በማቅረብ፣ የተማሪዎችን ፍላጎት ከግንዛቤ ባለማስገባት በራሳቸው አተያይ ብቻ በመሄድ፣ ለተማሪዎች ተገቢውን ውጤት በፍትሐዊነት አለመስጠት፣ ከተማሪዎች ጋር በተለያዩ ምክንያቶች በመጋጨት እና በመደባደብ፣ በቂ ዝግጅት አድርገው ወደ ክፍል አለመግባት፣ እርስ በእርስ እየተተካኩ ተማሪዎችን በማወክ፣ የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በአግባቡ ካለመጠቀም የተነሳ ጀማሪ መምህራን ወቀሳ ሲቀርብባቸው ይስተዋላል ፡፡ በሌላ በኩል አንዳንድ ነበር መምህራንም አልፎ አልፎ የዘመኑ ልጆች የማይፈልጉትን ከፍተኛ ቁጥጥር በማካሄድና ለስራቸው ካላቸው ተነሳሽነት ማጣት የተነሳ ወቀሳዎች ሲሰነዝሩባቸው እንደሚስተዋል ለመረዳት ተችሏል፡፡
- በነባር እና በጀማሪ መምህን መካከል ያለው የስራ መስተጋብር በሚመለከት፣ በየጊዜው የተለያዩ የልምድ ልውውጦች ይከናወናሉ፡፡ ነገር ግን ለይስሙላ እና አድርጌአለሁ በሚል ሪፖርት ለማቅረብ እንጂ አንዱ ከአንዱ እውቀት አገኛለሁ በሚል የሚከናወን እንዳልሆነ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይህም እርስ በእርስ ከመናናቅና እኔ ዓውቃለሁ ከሚል የተሳሳተ አመለካከት እና የግዴለሽነት ስሜት የመነጨ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

- ብዙ ጊዜ የቋንቋ መምህራን በተለይ ወጣቶቹ በዋናነት የተመረቁበትን ቋንቋን ከማስተማር ይልቅ በንዑስ (minor) የተመረቁበትን ሥነዜጋን ማስተማር መፈለጋቸው አንዳንዴ በክፍል ትምህርቱ ውስጥ ችግሮች ሲፈጠሩ ይስተዋላል፡፡
- ጀማሪ መምህራን ከተማሪዎች ጋር በመጋጨት፣ ለተማሪዎች በአግባቡ ውጤት ባለመስጠት፣ ተማሪዎችን በመደብደብ፣ ከፆታዊ ግንኙነት ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ስሞታዎች ሲቀርቡባቸው፣ በነባር መምህራን ለማስተማር ከመሰልቸት፣ ሙሉ ኃይልን ተጠቅመው ካለማስተማር የተነሳ አልፎ አልፎ ስሞታዎች እንደሚመጡ ገልፀዋል፡፡ በአንጻራዊ መልኩ ግን ነባር መምህራን የተለያዩ ምስጋናዎች እና ሽልማቶች በተማሪዎች ሲሰጣቸው እንደሚያስተውሉ ለመረዳት ተችሏል፡፡

4.2 ከመጠናዊ መረጃዎች የተገኘ ውጤት

የነባርም ሆነ የጀማሪ መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርት አተገባበር ደካማ እንደሆነ ቢረጋገጥም፤ ከጀማሪ መምህራን አተገባበር ግን የነባር መምህራን አተገባበር የተሻለ እንደሆነ ከሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች የተገኙ ውጤቶች አረጋግጠዋል፡፡ በሁለቱ የጥናት ተተኳሪዎች መካከል ጉልህ የአተገባበር ልዩነት መኖር አለመኖሩ በቲ-ስሌት ተፈትሾ፣ ከ18 ንዑሳን ተግባራት መካከል በ 2 ብቻ ጉልህ ልዩነት መኖሩ ሲረጋገጥ፣ በሌሎቹ ግን ጉልህ ልዩነት እንደሌለ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ደግሞ በነባር መምህራን እና በጀማሪ መምህራን መካከል የአንብቦ መረዳት ትምህርት አተገባበር ልዩነት ቢስተዋልም፤ ልዩነቱ ግን ጉልህ እንዳልሆነ የሚያመለክት ነው፡፡

የቅድመ ንባብ ተግባር በነባርም ሆነ በጀማሪ መምህራን በቂ ትኩረት የማይሰጠው የንባብ ደረጃ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ ምክንያቱም መከናወን ከሚገባቸው 18 አማካይ የቅድመ ንባብ ተግባራት፣ ነባሮቹ 10.5 አማካይ ውጤት ሲያስመዘግቡ፣ ጀማሪዎች ደግሞ 6.5 አማካይ ውጤት ብቻ አስመዝግበዋል፡፡ ከምልከታ እና ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ከተገኘው ውጤት መረዳት እንደተቻለው፡፡ ሁለቱም የጥናቱ ተተኳሪዎች የቅድመ ንባብ ትግበራቸው ደካማ ቢሆንም ከጀማሪዎቹ አተገባበር ግን የነባሮቹ የተሻለ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

በጊዜ ንባብ ወቅት መከናወን ከሚገባቸው 24 አማካይ የጊዜ ንባብ ተግባራት መካከል ነባር መምህራን 15 አማካይ ውጤት ሲያስመዘግቡ፣ ጀማሪ መምህራን ደግሞ 6.5

አማካይ ውጤት ብቻ አስመዝግበዋል፡፡ ከዚህ እና ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙ ውጤቶች እንዳመለከቱት እንደ ቅድመ ንባብ ሁሉ በጊዜ ንባብም ነባር መምህራን ከጀማሪ መምህራን የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

በድህረ ንባብ ደረጃ መከናወን ከሚገባቸው 12 ተግባራት መካከል ነባር መምህራን 10 አማካይ ውጤት ሲያስመዘግቡ፣ ጀማሪ መምህራን ደግሞ 7.75 አማካይ ውጤት አግኝተዋል፡፡ ከዚህ እና ከሌሎችም የመረጃ ምንጮች ከተገኘው ውጤት መገንዘብ የሚቻለው እንደ ቅድመ ንባብ እና ጊዜ ንባብ ደረጃዎች ሁሉ በድህረ ንባብ ደረጃም ነባር መምህራን ከጀማሪ መምህራን የተሻሉ እንደሆኑ ነው፡፡

በአጠቃላይ በጥናቱ እንደታየው የነባርም ሆነ የጀማሪ መምህራን የቋንቋ ትምህርት አተገባበር ችግር ያለበት እና ሁሉንም ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የማያስችል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከሁለቱ የጥናት ተተኳሪዎችም ሙሉ በሙሉ ነባር መምህራን ከጀማሪ መምህራን ተሸለው ተገኝተዋል፡፡ ይህም ከልምድ እና እውቀት ማነስ ብቻ የመነጨ ሳይሆን አዳዲስ መምህራን በሙያው ለመቆየት ካለመፈለግ፣ ከተማሪዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ጤናማ ካለመሆን፣ እና ለቋንቋ ትምህርት ዝቅተኛ ግምት ከመስጠት፣ ወዘተ. ጉዳዮች የመነጨ እንደሆነ ከነባር መምህራን እና ክፍለ ትምህርት ኃላፊዎች ጋር ከተካሄደ የቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ለእነዚህ እና መሰል ችግሮች ሌላ አዲስ ጥናት የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ ይህን ጥናት መሰረት አድርገው ወደፊት ሌሎች በዚህ ዙሪያ ጥናት እንዲያካሂዱ ሀሳቢን እየገለጽኩ የሚከተሉትን ጥቅል የመፍትሄ ሀሳቦች በመሰንዘር ጥናቴን በዚህ አጠቃልላለሁ፡፡

- በትምህርት ቤቶች የመምህራን አመዳደብ ላይ ነባርና ጀማሪ መምህራንን በእኩል በማሰባጠር ምደባ ቢካሄድ፣
- በነባርና ጀማሪ መምህራን መካከል የሚካሄደው የልምድ ልውውጥ ለይስሙላ ሪፖርት ለማቅረብ ሳይሆን ከልብ ለመነጨ መማማር እንዲሆን ክትትልና የማሳመን ስራ ቢሰራ፣
- በመምህራን መካከል የጋራ አስተሳሰብና አንድነት እንዳይጎለብት እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ እንደ ፖለቲካዊ፣ ሐይማኖታዊ ፣ ወዘተ. አይነት ጣልቃ ገብነቶችን ከትምህርት ቤት ማራቅ፣

- ለጀማሪ መምህራን በመማር ማስተማር አተገባበር ዙሪያ በአስገዳጅነት ላይ ሳይሆን በማሳመን ላይ የተመሰረተ ተከታታይ ስልጠናዎች ቢሰጡ፣
- ጀማሪ መምህራን ልክ አንደ ነባሮቹ ከተማሪዎቻቸው ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት አባታዊና እናታዊ ባህሪን የተላበሰ እንዲሆን ጥረት ቢደረግ፣
- ጀማሪ መምህራን የቀረበውን የትምህርት ይዘት በአግባቡ አስተምረው እንዲሸፍኑ ክትትልና ድጋፍ ቢደረግ፣
- ከአለ በቂ ዝግጅት የሚገቡ መምህራን በተለይም ጀማሪዎቹ ላይ ተገቢ ቁጥጥር ቢደረግ፣
- ጀማሪ መምህራን ማስተማር ማለት መማር መሆኑን ተረድተው እራሳቸውን በእውቀት እና በማስተማር ብቃት እንዲያጎለብቱ ቅስቀሳና ድጋፍ ቢደረግ፣
- ነባር መምህራን አዳዲስ እውቀቶችን እና የማስተማሪያ ዘዴዎችን ላለመቀበል ያላቸውን አመለካከት ለመቀየር ጥረት ቢደረግ፣
- ነባር መምህራን የዘመኑ ልጆች የማይፈልጉትን የሀይል ቁጥጥርን እንዲያሻሽሉ ቢመከርበት፣
- በመጨረሻም በዋናነት መምህራን ለሙያቸው ፍቅር እና አክብሮት እንዲኖራቸውና ይሄን ተከትሎ የማስተማር ተነሳሽነታቸው እንዲጨምር በተለያዩ ጥቅማጥቅሞች የማርካት ስራ ቢሰራ የተሻለ የትምህርት ጥራትን በትምህርት ቤቶች ማረጋገጥ ይቻላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ዋቢ ጽሑፎች

Abiyot Nega (2001) Pedagogical Challenges Among Fresh Instructors. Institute of Educational Research (IER) FLAMBEAU, 9(1), 1-7.

Amera Seifu (2005) The Contribution of Teachers' Perception, Interest, Teaching Experience and Field of Specialization to Educational Research Practices: Bahirdar University in Focus. The Ethiopian Journal of Education, xxv (2), 1-28.

Amera Seifu (2008) Teachers Difference on Utilization of Instructional Materials as the Functions of their Years of Teaching Experience, Level of Academic Qualifications, and School Contexts in Bahirdar Town Schools. The Ethiopian Journal of Education, XXVII (2), 101-128.

Azeb Desta (1984) Elements of General Methods of Teaching. Addis Ababa University (unpublished).

Crouch, C. (1989) An International Journal for Teachers of English to Speakers of Other Languages. English Language Teaching Journal, 43(2), 105-111.

Cullingford, C. (1995) The Effective Teacher. London: Cassell.

Dawit Asrat (2000) Concerns of Teachers with Respect to Experience, Sex and Qualification: The Case of Addis Ababa Region. Addis Ababa University: Unpublished (M.A. Thesis).

Jeylan Wolyie (2000) An Exploration of the Developmental Context of the Experienced English Language Teachers in the Senior Secondary Schools of Addis Ababa. Addis Ababa University: Unpublished (M.A. Thesis).

Marsh, H. (2007) Do University Teachers Become more Effective with Experience? A Multi Level Grwoth Model of the Students' Evaluation of Teaching. Journal of Educational Psychology, 99(4), 775-790.

Mesafint Muche (1999) The Impact of Expert Teachers and Their Teaching in an EFL Situation in Government Owned High Schools. Addis Ababa University (M.A. Thesis).

Nunan, D. (1992) Collaborative Language Learning and Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Palmer, C. (1993) Language Learning and Success: Studying through English. English Language Teaching Journal, 13 (1), 166-171.

Reada Darge (2005) Prospective Teachers' Sense of Efficiency and Beliefs about Managing Students: Implication for Professional Development of Teachers. The Ethiopian Journal of Education, XXV (2), 30-56.

Redwan Nuri (2006) Attitude of Students and Teachers Towards Plasma Instruction in Butajira and Silti Secondary Schools. Addis Ababa University: Unpublished (M.A Thesis).

Smith, W. (1982) Career Education Attitude and Practice of K-12 Science Education. Journal of Research in Science Teaching, 19 (5), 367-375.

Stern, H. (1983) Fundamental concept of Language Teaching. New York : Oxford university press.

Underhill, U. (1996) An Introductional Journal for Other Language. English Language Teaching Journal, 43 (4), 250-261.

Wingard, P. (1974) English Language Teaching. English Language Teaching Journal, XXIX(1), 46-52.

Yohannes Benti (2005) A Survey Study of In School Factors Affecting Quality of Education in Secondary Schools in Oromia. Addis Ababa University: Unpublished (M.A. Thesis).

አባሪ

በውይይት ወቅት የተነሱ ዋና ዋና ጥያቄዎች እና የተሰጡ መልሶች

1. ከጥናቱ የመፍትሄ ሐሳቦች መካከል ነባር እና ጀማሪ መምህራንን በትምህርት ቤቶች አመጣጥኖ መመደብ ያስፈልጋል የሚለውን በተግባር ላይ ለማዋል አያስቸግርም ወይ? እንዴት አድርጎ ነባሮችን አሳምኖ መመደብ ይቻላል?

   መልስ፡- አሁን ካለው የመምህራን አመዳደብ ልምድና አካሄድ አኳያ ስንመለከተው ያስቸግራል፡፡ ነገርግን የሚፈለገውን የትምህርት ጥራት በሁሉም ትምህርት ቤቶች በፍታሃዊነት ለማረጋገጥ እና የልምድ ልውውጥን በተገቢው መንገድ ለማካሄድ ግን የግድ ይህ አካሄድ መስተካከል አለበት፡፡

2. ጥናቱ በአንድ ክፍለ ከተማ ብቻ መካሄዱ ተገቢ ነው ወይ? ሌሎችንም ክፍለ ከተሞች ማካተት አልነበረበትም ወይ፡፡

   መልስ፡- የጥናትን ስፍት በሚወስኑት እንደ ጊዜ፣ ገንዘብ እና ቁሳቁስ አይነት ምክኒያቶች የተነሳ ነው በአንድ ክፍለ ከተማ ብቻ የተካሄደው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ወሳኝ ነገሮች ከተስተካከሉ ድጋሜ በስፋት ማጥናት ይቻላል፡፡

3. በጥናቱ ነባር እና ጀማሪ መምህራን የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ውጤትስ ምን እንደሚመስል ለምን በንጽጽር አልፈተሸም?

   መልስ፡- የጥናቱ ዓላማ የትምህርቱን አሰጣጥ ሂደት እንጅ የተማሪዎችን ውጤት መፈተሽ ላይ ያተኮረ ስላልነበረ በዚህ ጥናት አልታየም፡፡ በመሆኑም በሌላ ጥናት የተማሪዎች ውጤት በንጽጽር መጠናት ይኖርበታል፡፡

4. መምህሩ ለምን ለሙያው ፍቅር የለውም?

መልስ፡- አብዛኞቹ ተጠኞች ለሙያችን ፍቅር እንዳይኖራቸው ያደረገው በዋናነት በሚከፈላቸው ክፍያ ደስተኞች ስላልሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን ለሙያቸው ፍቅር እንዲኖራቸው በተለያዩ ጥቅማጥቅሞች የማስደሰት ስራ ቢሰራ ጥሩ ነው፡፡

5. ጀማሪ መምህራን ለምን በቂ ዝግጅት ሳያደርጉ ወደ ክፍል ለማስተማር ይገባሉ?

መልስ፡- አብዛኛውን ጊዜ ጀማሪ መምህራን በስራው ላይ ለመቆየት ያልወሰኑ እና ሌላ ስራ በመፈለግ ላይ የተጠመዱ በመሆናቸው እንደሆነ ነው በተጠኝዎች የተገለጸው፡፡

6. ጀማሪ መምህራን ለምን ተማሪዎችን ይደበድባሉ?

መልስ፡- ብዙውን ጊዜ ጀማሪ መምህራን ተማሪዎች በሚያጠፉበት ወቅት እንደ ነባሮቹ በምክር ከማስተካከል ይልቅ በሐይል እርምጃ ለማስተካከል የሚሞክሩት የወጣትነት ስሜታቸው እያሸነፋቸው ነው ተብሎ ይገመታል፡፡

7. የጥናቱ የመፍትሄ ሐሳብ መምህራን በኮሌጅ ቆይታቸው ስለነበራቸው የአሰለጣጠን ሁኔታስ ለምን አላመላከተም?

መልስ፡- የጥናቱ ትኩረት መምህራን በማስተማር ሙያ ላይ ከተሰማሩ በኋላ ስለሚስተዋልባቸው ክፍተት እና ጥንካሬ እንጅ ስለ ኮሌጅ ቆይታቸው የሚዳስስ አልነበረም፡፡

8. ነባር መምህራን የዘመኑ ልጆች የማይፈልጉትን የሀይል ቁጥጥር ይጠቀማሉ ሲባል እንዴት ነው?

መልስ:- እነሱ በሚማሩበት ወቅት የነበረውን እና በአሁኑ የትምህርት ፖሊሲ የተከለከለውን የተማሪ የቁጥጥር መንገድ ለማለት ነው፡፡

9. ጥናቱ ለምን ርዕሰ መምህራን እና የትምህርት ክፍል ሀላፊዎችን አልጨመረም?

መልስ:- ጥናቱ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደትን ብቻ የሚመለከት ስለነበረ ለማካተት አላስፈለገም፡፡

10. ለመምህራን ጥቅማ ጥቅሞች ቢሰጥ ሲባል ምን አይነት ጥቅማ ጥቅሞች ናቸው?

መልስ፡- የአገር ኢኮኖሚ የፈቀደውን ማነኛውም ነገር ቢሆን የሚል እምነት አለኝ፡፡